የሰበር መ.ቁ.16624

ጥቅምት 18 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፦ 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጐስ ወልዱ

4. አቶ ዳኜ መላኩ

5. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

አመልካች፦ ወ/ት እጅጋየሁ ተሾመ

መልስ ሰጭ፦ የአቴነሽ በቀለ ሞግዚት ወ/ሮ እታገኝ ዘነበ

ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ፍርድ ወይም ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ለሰጠው ፍርድ ቤት ስለሚቀርብ አቤቱታ- የፍትሐብሄር ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 6/1/

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ ውሳኔ የሰጠው ፍ/ቤት ውሳኔውን የሰጠው ሀሰተኛ የኑዛዜ ሰነድን መሰረት አድርጎ በመሆኑ ዳኝነት እንደገና እንዲታይ አመልካች ያቀረበችውን ጥያቄ ፍ/ቤቱ ጥያቄው

የቀረበው አመልካች ይግባኝ ካቀረበች በኋላ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም

በማለት ውሳኔ በመስጠቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

ውሳኔ፡- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡

1. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.6/1/ መሰረት ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ጥያቄው የሚቀርበው ይግባኝ ከመቅረቡ በፊት መሆን አለበት፡፡
2. በውሳኔው ላይ ይግባኝ ከቀረበ የይግባኙ መዝገብ ቢዘጋም ዳኝነት እንደገና እንዲታይ የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡

የሰበር መ/ቁ. 16624

ጥቅምት 18 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች:-አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጐስ ወልዱ

አቶ ዳኜ መላኩ

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች:- ወ/ት እጅጋየሁ ተሾመ ጠበቃው ቀርቧል።

ተጠሪ:- የእቴነሽ በቀለ ሞግዚት ወ/ሮ አታገኝ ዘነበ ቀርባለች።

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

ይህ መዝገብ ተከፍቶ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የአሁኗ አመልካች ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6 መሠረት እንደገና ዳኝነት እንዲታይ የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በሚል የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ሐምሌ ቀን 1996 ዓ.ም. ተጽፎ እንዲቀርብ ባደረገችው ማመልከቻ መነሻ ነው።

ከመዝገቡ ለመመልከት እንደተቻለው ክርክሩን በመጀመሪያ ያየው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሟቹ ወታደር በቀለ መኩሪያ ሚያዝያ 8 ቀን 1989 ዓ.ም. አድርጓል በተባለው ኑዛዜ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ታህሣስ 17 ቀን 1994 ዓ.ም. ባቀረበው የኑዛዜ ሰነድ ላይ የተመለከተው ፊርማ ተመርመሮ የተናዛዡ አለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ውድቅ በማድረግ ወስኖ ከቆየ በኋላ የኑዛዜው ተጠቃሚ ነኝ የምትለው የአሁኗ አመልካች ግንቦት 30 ቀን 1995 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ ፍ/ቤቱ ለሰጠው ውሣኔ መሠረት የሆነው ለፖሊስ ቴክኒክ ምርመራ ተልኮ እንዲመረመር የተደረገው የኑዛዜ ሰነድ ከፍ/ቤቱ መዝገብ ጋር የተያያዘው ትክክለኛው ሰነድ ሣይሆን በሀሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል በሚል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.6/1/ መሠረት እንደገና ዳኝነት እንዲታይ ባቀረበችው አቤቱታ ላይ የአሁኗ ተጠሪ መልስ እንድትሰጥበት ካደረገ በኋላ ሰኔ 29 ቀን 1996 ዓ.ም. በሰጠው ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.6/1/ መሠረት እንደገና ዳኝነት እንዲታይ አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለው የይግባኝ ቅሬታ ከመቅረቡ በፊት ነው። በቀረበው ጉዳይ ግን አመልካች ቀድሞ በተሰጠው ውሣኔ ላይ ለይግባኝ

ሰሚ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርባለች፡፡ የይግባኝ ቅሬታ አቅርባ ከቆየች በኋላ ይግባኙን በማቋረጥ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.6 መሠረት ዳኝነት ይታይልኝ የሚል ጥያቄ ልታቀርብ አትችልም በሚል ምክንያት ሳይቀበላት ቀርቷል፡፡

አመልካች የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.6/4/ ዳኝነት እንደገና ሊታይ ይገባል አይገባም በሚል ፍ/ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማለት አይቻልም ስለሚል ፍ/ቤቱ የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት የሚለውን በቀጥታ ለሰበር ችሎት ልታቀርብ ችላለች፡፡

በአመልካች በኩል የቀረበው አቤቱታ ከተመረመረ በኋላ እንደገና ዳኝነት ይታይልኝ ጥያቄ ተቀባይነት ያጣው በሕጉ አግባብ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ መወሰን ያስፈልገዋል ተብሎ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ማመለከቻውም ለአሁኗ ተጠሪ ተልኮ ደርሷት ቀርባ በጽሁፍ መልስ ሰጥታበት ተከራክራለች፡፡

ይህ ችሎት በበኩሉ ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ አይገባም የተባለው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6/1/ ማናቸውም ሰው ፍርዱን ወይም ውሳኔውን

ለሰጠው ፍ/ቤት እንደገና ዳኝነት እንዲታይ አቤቱታ ሊያቀርብ የሚችለው በተሰጠው ፍርድ ወይም ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ላይ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ ከማሰማቱ በፊት እንደሆነ ያስረዳል። በቀረበው ጉዳይ የአሁኗ አመልካች ፍ/ቤቱ አስቀድሞ በሰጠው ውሣኔ ላይ ለከፍተኛው ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርባ በፍ/ቤቱ ለምርመራ እያለ ሲቀጥር መቆየቱ ተረጋግጧል። የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የይግባኙን መዝገብ አስቀርቦ በተመለከተበት ጊዜ ሁሉ ይግባኙ በእንጥልጥል ላይ ነበር። አመልካች ይግባኙን አዘግቻለሁ የምትለው ፍ/ቤቱ የይግባኙን መዝገብ በማስቀረብ ለምርመራ ተበሎ መቀጠሩን በማረጋገጥ ከመለሰው በኋላ ነው። አመልካች ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሣኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ አቅርባለች አላቀረበችም የሚለው ጥያቄ ተነስቶ ማቅረቧ ከተረጋገጠ በኋላ ይግባኙን ለሚሰማው ፍ/ቤት መዝገቡ እንዲዘጋላት ጠይቃ አዘግታ መቅረቧ የይግባኝ ቅሬታ አላቀረበችም ለማለት የሚያስችል አይደለም። አመልካች ይግባኝ ማቅረቧ ከተረጋገጠ ከላይ በተጠቀሰው የሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት እንደገና ዳኝነት ይታይልኝ በሚል የምታቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት

አይኖረውም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍ/ቤት ቀደም ሲል በተሰጠው ውሣኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ቀርቦበታል በሚል ምክንያት እንደገና ዳኝነት ሊታይ አይችልም በሚል በሰጠው ብይን ተፈጽሟል የሚባል የሕግ ስህተት የለም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ በፍ/መ/ቁ.3324, ሰኔ 29 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጠው ብይን በፍ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡